**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ጊዜ፦ የ2018 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 034284**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ሥነ-ዜጋ

## ለአዲስ ገቢዎች

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א.ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב.የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና ሁለት ምዕራፎች አሉት።

ምዕራፍ አንድ — (2x32) — 64 ነጥብ

ምዕራፍ ሁለት — (3x12) — 36 ነጥብ

በአጠቃላይ — 100 ነጥብ

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד.ልዩ መመሪያ፦

ጥያቄውን ከመመለስህ በፊት በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተሰጠውን መመሪያ በጥሞና አንብብ።

ሥራህን በሙሉ በዚህ የፈተና ደብተር ላይ ብቻ ጻፍ። የፈተናውን ረቂቅ (טיוטה)፣ ርዕሶችንና የመሳሰሉትን በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የረቂቅ ገጽ ላይ "ረቂቅ"ብለህ ከላይ ጻፍበት። ማንኛውንም ረቂቅ በሌላ ወረቀት ላይ መጻፍ የፈተናውን ውድቅ መሆን ሊያስከትል ይችላል!

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ለሁለቱም ጾታዎች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ח, 2018

**מספר השאלון: 034284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# אזרחות

## לעולים חדשים

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה שני פרקים.

פרק ראשון —(32x2) — 64 נקודות

פרק שני —(12x3) — 36 נקודות

סה"כ — 100 נקודות

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. הוראה מיוחדת:

לפני שתענה, קרא בעיון את ההוראה בראש כל פרק.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).
רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች መካከል ሁለቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 32 ነጥብ)።

**1.** እስራኤል አገር — ይሁዳዊት አገር

ሀ. በነጻነቱ አዋጅ ላይ ይሁዳዊው ሕዝብ በምድረ እስራኤል ላይ ባለመብት መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች (ማሳመኛዎች) አሉ።
ከእነዚህ ማስረጃዎች ውስጥ ሦስቱን አብራራ። (12 ነጥብ)

ለ. **የመመለስ ሕግ** (חוק השבות) እንዴት የእስራኤል አገርን ይሁዳዊ ባሕሪይ እንደሚገልጽ አብራራ። (12 ነጥብ)

ሐ. እስራኤል አገር ከአገሪቱ ውጭ ካሉ ይሁዳዊያን (יהודי התפוצות) ጋር ያላትን ግንኙነት ጠብቆ ለመቀየት (ለማስጠበቅ) የምታደርጋቸውን ሁለት ድርጊቶች ጥቀስ። (8 ነጥብ)

**2.** የዲሞክራሲ አስፈላጊነት (עקרונות הדמוקרטיה)

ሀ. **የብዙሃን ውሳኔ መርሆ** (עקרון הכרעת הרוב) ምን እንደሆነ አብራራ። በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር የብዙሃን ውሳኔን መጠቀሚያ አንድ ምሳሌ አብራራ። (12 ነጥብ)

ለ. **የሃይማኖት ነጻነት** (חופש דת) መብት ምን እንደሆነ እና ከ**ሃይማኖት ነጻ የመሆን** (חופש מִדת) መብት ምን እንደሆነ አብራራ። (10 ነጥብ)

ሐ. **የፕሉራሊዝም መመሪያ** (עקרון הפלורליזם) በዲሞክራሲያዊ ምርጫዎች ላይ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን አብራራ። (10 ነጥብ)

**3.** የመንግሥት ባለሥልጣናት (רשויות השלטון)

ሀ. **በፓርላማው ኮሚቴዎች** (ועדות הכנסת) እና **በፓርላማው ምልአተ-ሸንጎ** (מליאת הכנסת) መካከል ያለውን አንድ ልዩነት አብራራ። (8 ነጥብ)

ለ. በእስራኤል አገር ያሉ የፍርድ ቤቶች ሦስት ደረጃዎችን ጥቀስ።
በሕግ ሥርዓት የተለያዩ ደረጃዎች ለምን እንዳስፈለጉ አብራራ። (12 ነጥብ)

ሐ. ከፊትህ ያለውን ክፍል አንብብ እና ቀጥሎ ባሉት ሁለት ጥያቄዎች ላይ መልስ ስጥ።
**የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ በእስራኤል አገር ውስጥ በሚገኙ ሆስፒታሎች ድንገተኛ ግምገማ አደረጉ። ወደ ሆስፒታሎቹ በማለዳ ወይም ከመሸ በኋላ በሌሊት በተለያዩ ሰዓቶች በመሄድ በድንገተኛ ክፍል እና በሌሎች ክፍሎች የሚሠሩ የሕክምና ሠራተኞች በጤና ጥበቃው ሚኒስትር መመሪያዎች መሠረት ይሠሩ እንደሆነ ገመገሙ።**
**የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩን ድንገተኛ ግምገማ ለምን እንደሚያደርጉ ሲጠይቋቸው የሆስፒታሎችን ትክክለኛ ገጽታ ለማግኘት በቀን ውስጥ በተለያዩ ሰዓታት ሆስፒታሎችን እንደሚጎበኙ፣ በሆስፒታሎች ውስጥ ምን እየሆነ እና እንዴት እየሠሩ እንደሆነ ለማወቅ ግዴታቸው እንደሆነ መልስ ሰጥተዋል።**

— ሚኒስቴራዊ ኀላፊነት (מיניסטריאלית) ምን እንደሆነ አብራራ።
— ሚኒስቴራዊ ኀላፊነት በክፍሉ ውስጥ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን አብራራ።

(12 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (36 ነጥብ)

ከ4-8 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

4. **ዜጎች** (**אזרחים**) መንግሥትን/ባለስልጣንን መገደብ የሚችሉበትን ሁለት መንገዶች አብራራ።

5. በእስራኤል አገር ውስጥ የድሩዚን ማህበረሰብ (העדה הדרוזית) ሁለት መለያዎች አብራራ።

6. በፓርላማዊ አገዛዝ (משטר פרלמנטרי) እና በፕሬዚዳንታዊ አገዛዝ (משטר נשיאותי) መካከል ያለ አንድ ልዩነት አብራራ።

7. የሚከተሉትን ሁለት ጽንሰ-ሐሳቦች አብራራ፦
   - የፍትህዊ ሂደት መብት (הזכות להליך הוגן)
   - የሃገር አስተዳደር ቁጥጥር (מבקר המדינה)

8. ቀጥተኛ ዴሞክራሲ (דמוקרטיה ישירה) እና ተወካይ ዴሞክራሲ (דמוקרטיה ייצוגית) ምን እንደሆነ አብራራ።

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך